ረቂቁ ተሻሽሎ የተፃፈው በ 9፣21፣2020 ነው

**የ King County Metro የቀረበው በጀት የክልሉን አውታረመረብ ይጠብቃል፣ ለወደፊቱ እድገት ወደፊት ይመለከታል**

የ King County ሥራ አስፈፃሚ Dow Constantine የክልሉን ትልቁ የህዝብ ማመላለሻ አውታር ሥራዎችን በገንዘብ ለመደገፍ መደበኛ ሂደቱን በመጀመር በሴፕቴምበር 22 ቀን ለ Metro የቀረበውን የሁለት ዓመት በጀት ለ King County ምክር ቤት አስተላልፏል፡፡

በጀቱ አስተማማኝ አውቶቡስ፣ water taxi (የውሃ ታክሲ)፣ access paratransit (አክሰስ ፓራትራንዚት) እና የ vanpool (ቫን ፑል) አገልግሎት ለመስጠት ቀጣይ ቁርጠኝነትን ያሳያል - በተለይም ፍላጎቶች በጣም ከፍተኛ የሆኑባቸው ተጓዦችን ለማገልገል፡፡

Metro በ COVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት ለቀነሱት የገቢ ትንበያዎች እና ለዝቅተኛ ተጓዦች ቀጣይነት ያላቸውን ተግዳሮቶች ምላሽ ለመስጠት እና ለማላመድ እንዴት እንዳቀደ ያሳያል፡፡

የመንቀሳቀስ ኔትወርክ ቀጣይ እድገት እንዲኖረው በጀቱ ተጓዦች እና ገቢዎች ሲያገግሙ Metroን ለማዘጋጀት ይረዳል፡፡

ከአስቸጋሪ የገንዘብ እውነታዎችን ጋር ስንጋፈጥ አንዳንድ ማስተካከያዎች በ 2021 እና 2022 አስፈላጊ ናቸው፡፡ ሆኖም፣ እኛ የአውቶቡስ አገልግሎት ለደንበኞቻችን ለማድረስ ቆርጠን እንደተሰጠን አለን፣ ዛሬ በመላው King County ወደ 11,000 የሥራ ቀናት የአውቶቡስ ጉዞዎች የሚሆን እእሰጠን ነው፡፡ እንዲሁም በወረርሽኝ ሳቢያ ከፍተኛ የመጓጓዣ የጉዞ ፍላጎት ለጊዜው በቀነሰበት የቀኑን ሙሉ ሰፊ አገልግሎት በመስጠት ላይ አተኩረናል፡፡

በአጠቃላይ፣ የወጪ አወጣጣችን ቅድሚያ አሰጣጥ ክልሉ ምላሽ ሲሰጥ እና ሲያገግም በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን ለደህንነት፣ ለእኩልነት፣ እና ለዘላቂነት ያለንን ቁርጠኝነት ያሳያል፡፡

Metro የትራንዚት አገልግሎትን ወደነበረበት ለመመለስ እና እንደገና ለመገንባት፣ የክልላችንን የካርቦን አሻራ ለመቀነስ እና የነጠላ ይዞታ ጉዞዎችን ለመቀነስ እየሰራ ነው፡፡ እኛ የፖሊስ ስራችንን እና የጉዞ አስፈፃሚዎቻችንን እንደገና እያሰብን ነው፣ እናም ቀጣይነት ባለው ተመጣጣኝ የዋጋ ክፍያ ለውጥ ላይ እንሰራለን፡፡

በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ትኩረት የሚሹ በርካታ ነጥቦች አሉ፡፡

**በ 2021-22 መገንባት እና ማድረስ**

- የ RapidRide H Line ን (የዛሬ Route 120ን በ Burien፣ White Center፣ Delridge፣ እና በሲያትል መሃል ከተማ መካከል) የ RapidRide G Line በሲያትል እና የወደፊቱ RapidRide I Line (Renton፣ Kent፣ እና Auburn)ን ለመጀመር አካሄዳችንን እንቀጥላለን፡፡
- በ 100% ዜሮ-ልቀት መርከቦች ላይ መዋዕለ ንዋያችንን ማዋል እንቀጥላለን እናም የመጀመሪያ ዙራችንን አዲስ ትውልድ 40 መጠን ባትሪ ያላቸው ኤሌክትሪክ አውቶቡሶች እና ተያያዥ የኃይል መሙያ መሠረተ ልማት ለመቀበል በዝግጅት ላይ ነን፡፡
- U District፣ Roosevelt፣ እና Northgateን በሲያትል ውስጥ ለማገልገል በ 2021 በሶስት አዳዲስ የታቀዱ የLink light rail ጣቢያዎችን ለማገናኘት በሰሜን King County ውስጥ የአውቶቡስ አገልግሎትን እንደገና ለማዋቀር ፅንሰ-ሀሳቦችን እያጠናቅቅን ነው፡፡
- ፍላጎቶች በጣም በሚበዙበት ቦታ አገልግሎትን ወደነበረበት እንመልሳለን፣ ለከፍተኛ ጉዞዎች/የተጨናነቁ መንገዶች፣ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው እና Black, Indigenous, and people of color (BIPOC፣ ጥቁር፣ የሀገሩ ተወላጅ፣ እና የቀለም ሰዎች) ማህበረሰቦች አገልግሎት የሚሰጡ ሀብቶችን እንመድባለን፡፡
- አሰሪዎች ስራዎችን መልሰው ሲያመጡ እና የጉዞ ዘይቤዎች ሲሸሻሉ አገልግሎትን በማስተካከል የክልሉ ኢኮኖሚ እንዲያገግም እንደግፋለን፡፡

**የፖሊስ ስራ እና ደህንነትን እንደገና ማገናዘብ፣ የዋጋ ተመን አወቃቀር**

- በስራ አስፈፃሚ Constantine እንደተገለጸው፣ Metro ከ King County የሸሪፍ ጽሕፈት ቤት፣ ሥራ ተቋራጮች፣ ሠራተኞችን እና ከማህበረሰቡ አባላት ጋር በመተባበር በቀለም ተጓዦች ላይ ያልተመጣጠነ አሉታዊ ተጽዕኖ ካሳደረባቸው የባህላዊ ክፍያ ማስፈጸሚያ አዳዲስ አማራጮችን በጋራ ይፈጥራሉ፡፡ በ COVID-19 አማካኝነት የክፍያ አፈፃፀም ቢያንስ እስከ 2020 መጨረሻ ድረስ መታገዱን ይቀጥላል፡፡ ዓላማው በ 2021 አዳዲስ ፕሮግራሞችን መንደፍ እና ከ 2022 በፊት ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

- Metro ኢኮኖሚው መልሶ እንዲያገግም ጊዜውን እንዲወስድ እንዲሁም የአውቶቡስ፣ የውሃ ታክሲ፣ የፓራትራንዚት አገልግሎት እና ሌሎችንም ጨምሮ በሁሉም የመንቀሳቀሻ መንገዶች ላይ የዋጋ ተመን እንዲከለስ የታቀደውን የመሳፈሪያ ጭማሪ ያዘገያል።

## አገልግሎትን ለማሻሻል እና ለማስተካከል የረጅም ጊዜ እቅዶች

የክልል Sound Transit Link light rail ዝርጋታዎች እየተከናወኑ እና የአውቶቡስ ፈጣን የመተላለፊያ ፕሮጀክቶች ወደፊት ሲጓዙ፣ Metro በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ የዕቅድ እና ተሳትፎ ሥራዎች ላይ ከደንበኞች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ ለመስራት በዝግጅት ላይ ነው፡፡ ጥረቶቹ ደንበኞች የሚተማመኑበትን ትስስር በማምጣት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የአውቶብስ፣ የባቡር፣ እና ፈጣን የመጓጓዣ ፕሮጀክቶችን ለማቀናጀት ከዚህ በፊት በተከናወነ ስኬታማ ሥራ ላይ ይገነባሉ፡፡ ***መሰረታዊ መስፋፋቶች፡-*** ወረርሽኙ እና በቤት-ይቆዩ የሚለው ትዕዛዝ የአገልግሎት ፍላጎትን፣ እንዲሁም ትንበያዎችን በእጅጉ ቀንሷል።

- የ South Annex Base ዲዛይን እና ግንባታን እስከ 2027 ድረስ ጨምሮ፣ Metro በ Tukwila South Campus ን ማስፋፋትን እየቀጠለ ነው፡፡ Metro ኤሌክትሪክ መርከቦችን በሙሉ በረጅም ጊዜ በመጠቀም ለአከባቢው ማህበረሰብ ለአካባቢያዊ እና ለአካላዊ ደህንነት አስተዋጽኦ ለማድረግ እነዚህን አዳዲስ ተቋማት ዲዛይን ያደርጋል፡፡ ሙሉ የኤሌክትሪክ South Campus መገልገያዎች ከአውቶቡስ የመሠረት ሥራዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ብክለት እና የድምፅ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ይረዳሉ፡፡ ከእኛ እኩልነትና ዘላቂነት መርሆዎች ጋር የሚጣጣሙ ለእነዚህ የአካባቢ እና ማህበረሰብ ግቦች ቁርጠኛ ነን፡፡
- በደቡብ King County ውስጥ አዲስ መሰረት ለመገንባት ጣቢያ ለመፈለግ Metro ጥረቶችን አግዷል፡፡ Metro በእነዚህ እርግጠኛ ባልሆኑ ጊዜያት ተለዋዋጭ ሆኖ ለመቆየት አቅዷል፣ እና ፍላጎቱ ሲመለስ ለደቡብ King County መሰረት የማግኘት ሂደቱን እንደገና ለማደስ እናስባለን፡፡

***RapidRide ለውጦች፡-*** በተቀነሰ የገንዘብ ሀብት ምክንያት፣ Metro ቀደም ሲል የታቀደውን የRapidRide ፕሮግራም መጠን በ 2027 ከሰባት መስመሮች በ 2027 ወደ ሦስት ወይም አራት ይወርዳል ብሎ ይጠብቃል፡፡ እነዚህ እምቅ ቅነሳዎች በ Metro Mobility Framework (ተንቀሳቃሽነት ማዕቀፍ) መረጃ የተሰጡ ናቸው፤ Service Guidelines (የአገልግሎት መመሪያዎች); እና የእያንዳንዱ ፕሮጀክት ሁኔታ፣ አደጋ፣ የአሠራር ወጪዎች እና የካፒታል ወጪዎች። በኖቬምበር ውስጥ የ King County ምክር ቤት በጀት ለመቀበል የመጨረሻ ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ነው፡፡

- በቀጣይ፣ ሁለቱም የ RapidRide G Line (Madison Valley - ሲያትል መሃል ከተማ) እና H Line (ሲያትል መሃል ከተማ-Burien) ፕሮጀክቶች የግንባታ ቀናት እየተቃረቡ ሲሆን በቶሎ ተግባራዊ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ እነዚህ መስመሮች እስካሁን ድረስ በየራሳቸው ፕሮጀክቶች መግባታቸው/መካተታቸው በ Metro እና በ Seattle Department of Transportation (SDOT) (የሲያትል ትራንስፖርት ክፍል) ኤጀንሲ ለረጅም ጊዜ ቅድሚያ የማግኘታቸው ውጤት ነው፡፡ በእንዲህ እንዳለ፣ የ G እና የ H መስመሮች በ 2021-2022 በቀረበው በጀት ውስጥ ተካትተዋል፡፡
- የ RapidRide I (Renton – Kent – Auburn)፣ J (ሲያትል መሃል ከተማ – Roosevelt)፣ K (Totem Lake – Eastgate), እና R (ሲያትል መሃል ከተማ – Mount Baker – Rainier Valley) መስመሮች በሙሉ ልዩ ፕሮጀክቶችን እና የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ይወክላሉ፡፡ እነሱ የ RapidRide ማስፋፊያ ፕሮግራም ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የኤጀንሲ ቅድሚያዎች ነበሩ እናም ከወደፊቱን የእጩ መተላለፊያዎች እጅግ ጠንካራውን የሚወክል ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በ I መስመር ላይ የሚሰሩ ሥራዎች እንደታቀደው ይቀጥላሉ፣ Metro ደግሞ በ J መስመር የሚኖረውን የ SDOT ጥረት ይደግፋል፡፡ በ K እና R መስመሮች ላይ ያለ የሜትሮ ሥራ ይቆማል፡፡

በሚመጡት ወራት የ King County ምክር ቤት በ "Executive Proposed 2021-22 Budget (ሥራ አስፈፃሚ ያቀረበው የ 2021-22 በጀት)" ላይ ተመልክቶ ድምጽ ይሰጣል፡፡ እነዚያ የመጨረሻ ውሳኔዎች ሲገኙ Metro ሪፖርት ያደርጋል፡፡ የሕዝብ አስተያየት የማግኘት ዕድሎችን ጨምሮ በበጀቱ ሂደት ላይ መረጃ ለማግኘት የ King County ካውንስል "2021-22 Biennial Budget" webpage (2021-22 ዓመታዊ በጀት" ድረ-ገጽን) ይጎብኙ።

ተጓዦች ለዕለት ተዕለት የጉዞ ፍላጎቶቻቸው እና አስተማማኝ፣ ዘላቂ፣ እና ፍትሃዊ የክልል የመተላለፊያ አውታረመረብን ለማቅረብ ሁላችንም በምንወስዳቸው እርምጃዎች በ Metro ላይ ያላቸውን አመኔታ እናደንቃለን፡፡

## የምክር ቤት ሂደት እና የስብሰባ ጊዜዎች

የምክር ቤቱ እይታ የ 2021-22 በጀት በማፅደቅ እስከ ኖቬምበር አጋማሽ ይጠናቀቃል። ህዝቡ ስለበጀቱ የተለያዩ ገጽታዎች አስተያየት በመስጠት በሂደቱ እንዲሳተፍ ይበረታታል፡፡ ምክር ቤቱ በበጀት ሂደት ውስጥ በተጨማሪ መረጃዎች ይህንን ገጽ ያዘምናል፡፡ በ COVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት፣ የምክር ቤቱ የበጀት ሂደት በመስመር ላይ ይካሄዳል።

ረቂቁ ተሻሽሎ የተፃፈው በ 9፣21፣2020 ነው

በማጓጓዣ ዙሪያ የበጀት ውይይቱን ለመከታተል ፍላጎት ካለዎት በ **ኦክቶበር 15 ቀን 2020 ከ 9:30am - noon (እኩለ ቀን)** በሚካሄደው ውይይት Metro የምክር ቤቱ የክልል ክብ ጠረጴዛ አካል ይሆናል። ስብሰባውን በቀጥታ በመስመር ላይ ማየት ይችላሉ እዚህ ወይም የ King County ቴሌቪዥን ቻናል 22 (Comcast ቻናል 22 እና 322 (HD) ፣ Wave Broadband ቻናል 22)ን በቀጥታ ማየት ይችላሉ።

በሚቀጥሉት የምክር ቤት ስብሰባዎች ህዝቡ አስተያየት የመስጠት እድል ይኖረዋል፡

- ሴፕቴምበር 30 (ረቡዕ) 9:30am – 12:00pm
- ኦክቶበር 22 (ሐሙስ) 6:00pm – 8:00pm
- ኖቬምበር 12 (ሐሙስ) 9:30am – 12:00pm
- ኖቬምበር 17 (Tuesday) 11am – 12:30pm - ይህ የበጀት ውይይቶች የመጨረሻ ቀን ነው፡፡
-

ማስታወሻ:- ስብሰባዎች ከተለጠፈው የመጨረሻ ጊዜ በተጨማሪ ሊቀጥሉ ይችላሉ። የስብሰባ አጀንዳዎች እዚህ ሊገኙ ይችላሉ እና የስብሰባ ቁሳቁሶች እዚህ ሊገኙ ይችላሉ።

**የህዝብ አስተያየት እንዴት እንደሚሰጥ**

በስብሰባው ወቅት የቃል የህዝብ አስተያየት መስጠት ይችላሉ እና አስቀድመው ለመመዝገብ አይጠየቁም፡፡

የስልክ ቁጥር፡- 1 253-215-8782

የስብሰባው መታወቂያ ቁጥር 995 4088 8432 ነው፤ የይለፍ ቃሉ 091270 ነው፡፡

(በስብሰባው ወቅት ለህዝብ አስተያየት እንዲጠሩ የማይፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ ስልኩን ከመጠቀም ይልቅ ስብሰባውን በመስመር ላይ ወይም በቴሌቪዥን ይመልከቱ።)

**ትርጉም**

ስለታሰበው በጀት የበለጠ ለመረዳት፣ እዚህ ጠቅ ያድርጉ። እዚያ በበርካታ ቋንቋዎች የበጀት መረጃን ያገኛሉ፡፡

**ማስተርጎም**

በሕዝብ አስተያየት ወቅት ለመመስከር ፍላጎት ካለዎት እና አስተርጓሚ ከፈለጉ እባክዎን፣ ስብሰባው ከመካሄዱ ቢያንስ 48 ሰዓታት በፊት Reeni Nair ን ያነጋግሩ፡፡

Ashreeni (Reeni) Nair

King County ምክር ቤት፣ የእኩልነት እና ማህበራዊ ፍትህ አስተባባሪ

206-477-4978

Reeni.Nair@kingcounty.gov

**ADA (ኤ.ዲ.ኤ) ፍላጎቶች**

ስብሰባዎች በመግለጫ ጽሑፍ ይዘጋሉ። ስብሰባውን ለማግኘት ተጨማሪ እርዳታ ከፈለጉ ወይም ምስክርነትዎን በጽሑፍ ለማቅረብ ከፈለጉ እባክዎን የጸሐፊውን ቢሮ በ clerk@kingcounty.gov ያነጋግሩ።